የኢትዮጵያ ብሔራዊ አንድነት አርበኞች ግንባር
(ኢ.ብአአግ)

Ethiopian National United Patriotic Front
(ENUPF)

June 28, 2006

# ከኢትዮጵያ ምድር ከትግል ሜዳ የተሰጠ መግለጫ!

መላው የኢትዮጵያ ሕዝብ ለዲሞክራሲና ለአንድነት የሚያደርገው ትግል በተፋፋመበት በአሁኑ ወቅት ጠላት ትግሉን ለመከፋፋል በሚያዘጋጀው ወጥመድ ውስጥ ላለመግባት ከፍተኛ ጥንቃቄ ማድረግ ያስፈልጋል። ይህንን ጥንቃቄ ሳያደርጉ ራስን ለጠላት ወጥመድ ማመቻቸት አውቀውም ሳይሆን ሳያውቅ የጠላት ተባባሪ መሆንን ያመለከታል። በተለይ በአርበኞች ላይ ከባድ ወንጀል የፈፀሙና በማይታወቅበት ሃገር በአውሮፓ፥ በአሜሪካና በአፍሪቃ እየተዘዋወሩ በአርበኞች ስም የሚነግዱ የተወሰኑ ግለሰቦች የጠላት መሣሪያ በመሆን ተቀጥረው ኢትዮጵያ ወደማያባራ ትርምስ ውስጥ እንድትገባ ለማድረግ የሚጥሩትን ወንጀለኞች ለይቶ በማወቅ የኢትዮጵያ ሕዝብ በየመድረኩ ሊታገላቸው፥ ሊያገላቸውና ሊያጠፋቸው ይገባል። ዛሬ እኛ ከኢትዮጵያ የተለያዩ ብሔረሰቦች አብራክ የወጣን ልጆቻችሁ፥ ወንድሞቻችሁ እና እህቶቻችሁ ሕይወታችንን መስማዕት ለማድረግ ተዘጋጅተን ሀሩሩን፥ ርሃቡን፥ ጥማቱንና በሽታውን ተቋቁመን በየበረሃው እየተዘዋወርን የወያኔን አረመኔ አገዛዝ ለመደምሰስና ዲሞክራሲያዊ ኃይሎች ሥልጣን እንዲጨብጡ ለማድረግ የተፋፋመ ትግል በምናደርግበት በአሁኑ ወቅት በአገር ውስጥና ከአገር ውጭ ካሉ ኢትዮጵያውያን የምንጠብቀው የተባበረ ድጋፋቸውን ነው።

ስማችን ከኢትዮጵያ ብሔራዊ አንድነት አርበኞች ግንባር ጋር ተዋህደንና ተባብረን የምንታጋል የኢትዮጵያ ሕዝብ አርበኞች ግንባር ስንሆን ብሔራዊ ሆነ ሕዝባዊ ትግሉ አንድ ነው። አመራሩም አንድ ነው። በሜዳ የምንገኘው የፈጠርነው አንድ ግንባር ነው። ለኢትዮጵያውያን ሁሉ ባሉበት በሙሉ እምነትና ሃቅ ልናረጋግጥ የምንፈልገው ሃቅች አሉን። እዚህ በሃገር ውስጥ በሜዳ የሚታገለውና የሚዋጋው የኢትዮጵያ ሕዝብ አርበኞች ግንባርና ከኢትዮጵያ ውጭ በሎጂስቲክ አቅርቦት፥ በፖለቲካና በአመራር የሚያታግሉን የኢትዮጵያ ብሔራዊ አንድነት አርበኞች ግንባር ተባብረውና ተዋህደው በአንድነት መታገላቸው ነው። መዋቅሩም የተጠነሰሰው ከዚህ ዓለም በሞት በተለዩት በኢንጂነር ቅጣው እጅጉ፥ በአርበኛው ተስፋዬ ጌታቸውና በሃገር ወዳድ ኢትዮጵያውያን ነው። እነዚህም ክፍሎች እየተደገፉ ትግሉን ወደ ወሳኝ ደረጃ እያሸጋገሩት ነው።በኢትዮጵያ ሕዝብ አርበኞች ግንባር ስም ሌላ ታጋይ ሠራዊት አለ ብሎ የሚያምን ካለ ሜዳው ድረስ መጥቶ ማረጋገጥ ይቻላል። ከዚህ ሃቅ ውጪ ሠራዊት አለን እያሉ በእኛ ስም የሚነግዱ ገንዘብ የሚያሰባስቡ ካሉ አጭበርባሪዎች ናቸው። አርበኛው ሊፋደዳቸው የሚፈልግ ብዙ ግፍና ወንጀል የፈጸሙ አርበኛውን ለከፋፋያችን ለኢትዮጵያ ጠላቶች መሳሪያ ለማደርግ የሚሞክሩ በአውሮፓና በአሜሪካ እየተዘዋወሩ የሚነግዱ የሻቢያ ምንደኞች ምንጊዜም የእኛን ፊት ለማየት እንደማይችሉ ያውቁታል፤ ጊዜ ሳያልፍ ያኔ እንፋረዳቸዋለን። ይህንን በተመለከተ ዋሸተንና ቀጥፈን እንደሆነ የኢትዮጵያ ሕዝብ ወደፊት እንደሚፋረደን ግልጽ ነው።

ENUPF Development Foundation. North America Headquarters
P. O. Box 984, Tucker, GA 30085 • U.S.A. •
Tel. (404) 394-4321 • Fax (770) 414-0061
www.enupfforethiopia.org

ስለዚህ ዛሬ የነገርናችሁ እውነት ስለሆነ እውነቱን አውቃችሁ ከአጭበርባሪዎች እርቃችሁ እርዳታችሁንና ድጋፋችሁን በአንድ እውነተኛ አቅጣጫ አድርጉት።

ሁለተኛ ይህንን ወሳኝ ትግል በማካሄድ ላይ የምንገኝ የኢትዮጵያ ሕዝብ አርበኞች ግንባር ሥር የተሰበሰበው ፍፁም ኢትዮጵያዊ የሆነ ሠራዊታችሁ በኤርትራ መንግሥት ሆነ ከሌሎች ጐረቤት አገሮች ጥላ ሥር ያልተደራጀና ከኢትዮጵያዊነት ውጪ የሌላ የማንንም ጥቅም የማያራምድ በኢትዮጵያ አንድነትና ሉኡላዊነት የጠራ አቋም ያለው ግንባር ነው።

በዚህ አርበኞች ግንባር ሥር የተሰበሰበው ለኢትዮጵያ ሕዝብ አንድነትና ነፃነት የምንዋጋው ገንፍሎ የመጣውን የኢትዮጵያን አርበኝነት ስሜት የምንወክል ለማንም ከፋፋይ ኃይል የማናጐበድድ የኢትዮጵያ አርበኞች ከጥንት ጀምሮ የተዋጋለትንና የሞትለትን ዓላማ ከግቡ ለማድረስ የምንሰዋው አኩሪ ወገናችሁ ነን።

የኢትዮጵያ ሕዝብ የምለምነውና የምንጠብቀው ለዚህ ክብር ዓላማ ደም በዚህ ስም የምንታገለው ግንባር አንድ ብቻ መሆኑን በግንባሩ ስም የተሰበሰበ ሌላ ሠረዊት በኢትዮጵያ ትግል ሜዳ አለመኖሩን እንድታውቁ ነው። ይህ ቃላችን በደማችንና በአጥንታችን የሚረጋገጥ የእውነት ቃል ነው።

ድጋፋችሁ አይልየን

ኢትዮጵያ በጀግኖች አርበኞችና በእግዚአብሔር ኃይል ነፃነቷን ታገኛለች!!